ክፍል ተመሳሳይ በሆነውና በሉቃስ ወንጌል ላይ በሚገኘው የትምህርት ክፍል ላይ ጌታ አንድ ሌላ ምሳሌ በመጠቀም እንዳስተማረ እናገኛለን፡፡

> «ከእናንተ ማናቸውም ወዳጅ ያለው፣ በእኩለ ሌሊትስ ወደ እርሱ ሄዶ፣ ወዳጄ ሆይ፣ ሦስት እንጀራ አበድረኝ፣ አንድ ወዳጄ ከመንገድ መጥቶ የማቀርብለት የለኝምና ይላልን? ያም ከውስጥ መልሶ፣ አታድከመኝ አሁን ደጁ ተቆልፏል፣ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ፣ ተነስቼ ልሰጥህ አልችልም፤ ይላልን? እላችኋለሁ ወዳጅ ስለ ሆነ ተነስቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው ተነስቶ የሚፈገውን ሁሉ ይሰጠዋል፡፡ እኔም እላችኋለሁ፣ ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ፣ ታገኙማላችሁ፣ መዝጊያን አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል፡፡ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፣ የሚፈልግም ያገኛል፣ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል፡፡ አባት ከሆናችሁ ከማናችሁም ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፣ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሳ ደግሞ ቢለምነው በዓሳ ፈንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይንስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ በሰማይ ያለው አባት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን አይሰጣቸው» /ሉቃ11፡5-13/

እንግዲህ በጌታ ፊት በመፈለግ፣ በመለመንና በማንኳኳት ጊዜ የምንወስድበት ምክንያት ሌላ ሳይሆን ጌታ ራሱ በዚህ ሁኔታ እንድንቀርብ ስለወደደ ወይም ስለፈለገ ነው፡፡ ከዚያም ባለፈ ይህ ጸሎታችን የሚያስተላልፈው መልዕክት፣ በጌታ ላይ ያለንን መታመን፣ መደገፍና መመካትን ነው፡፡

እግዚአብሔር መለመንና ማንኳኳታችንን ብቻ ሳይሆን፣ ከልብ የሆነ ፍላጎታችንን ያያል፡፡ ምክንያቱም እርሱ ጨዋ አምላክ ነው፤ ማንንም ያለ ፍላጎቱ አስገድዶ አንዳች ማድረግ አይሻም፤ ለዚህ ነው የሰውን ፍላጎት አጥብቆ የሚፈልገው፡፡ እኔ እንኳ በአቅሜ ሐዘን የደረሰበትን ሰው የማጽናናት ዕድሉን ሳገኝ ከሁሉ አስቀድሜ ሐዘንተኛውን የምጠይቀው፣ *«ለመጽናናት ፍቃደኛ ነህ ወይ?»* ብዬ ነው፡፡ ይህንን የማደርገው ምናልባት ሰውየው ከልቡ የሚያምነው ጠንካራ ሐዘን ማዘን እንዳለበት ከሆነ፣ የሚፈልገውም እንዲያ እንዲሆንለት እንደሆነ ስለምረዳ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በተለይ በእኛ በኢትዮጵያውያን ባህል በአብዛኛው ማለት ይቻላል፣ ሐዘንን ማጥበቅ እንደ ዋነኛ ነገር ተደርጎ ነው የሚታሰበው፤ ታዲያ ፍላጎቱና እምነቱ በሌለበት ሁኔታ አንድን ሰው ለማጽናናት መሞከር ትርፉ ድካም ብቻ መሆኑ አይቀርም፡፡ ልክ እንደዚሁ ጌታ መንፈስ ቅዱስም ለማጽናናት የሚፈቅደው ለመጽናናት የሚፈልጉትን ነው፡፡ እርሱ ለእኛ አንዳች ነገር ለማድረግ የልብ ፍላጎታችንን አጥብቆ ይሻዋል፡፡

ማንም መንፈሳዊ ሰው፣ በተራራው ስብከት ላይ ጌታ ያስተማራቸውን «የዳነ ክርስቲያን የሕይወት ወግ» ሲሰማ ወይም ሲያነብ ከልቡ አንዳች የመሆን ወይም የመለወጥ ቅናት መቀጣጠሉ እንደማይቀር አስባለሁ፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ጊዜ ይህ የመሆን ፍላጎትና ተስፋ ጊዜአዊና ዘለቄታነት የሌለው ሆኖ እንዳይገኝ ፍላጎቶቻችንን በጥልቅና ጠንካራ ልመናና ማንኳኳት ማጀብ መቻል አለብን፡፡ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእኛ የሚሠራ ጌታ ይረዳናል፡፡/ፊል2፡13/



## ወርቃማው መመሪያ 7፡12

> እንግዲህ ሰዎች ሲያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና፡፡

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ትምህርት ባስተማረበት ዘመን አይሁድ *«ሰዎች እንዲያደርጉብህ የማትሻውን አንተም በእነርሱ ላይ ከማድረግ ተቆጠብ»* የሚል ሃይማኖታዊ መመሪያ ነበራቸው፡፡ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረው የሥነ ምግባር መመሪያ ግን ከዚህ እጅግ የላቀ ስብእናን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ሰዎች ለእኛ እንዲያደርጉልን የምንሻውን ሁሉ ለሌሎች የማድረግ ኃላፊነት ነው፡፡ በዚህም ደግሞ የሕግና የነቢያት ትምህርትና ትዕዛዝ ሁሉ ተጠቃሏል፡፡ ከዚህ የተነሳ ይህን ትዕዛዝ ብዙ የነገረ መለኮት ተማሪዎች «ወርቃማው ሕግ» በማለት ሊጠሩት ችለዋል፡፡

ይህ ወርቃማ ሕግ፣ እግዚአብሔር አምላክህን፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ኃይልህ፣ በፍጹም አሳብህ፣ በፍጹም ነፍስህ ውደድ፣ ከሚለው ትዕዛዝ እና ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ ከሚለው የብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ትስስር ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው አምላኩን በዚያ ሁኔታ ከወደደ ጌታ ለፈጠራቸውና ለሚወዳቸው የሰው ልጆች ያለው አመለካከትና አስተሳሰብ ፍጹም መቀየሩ አይቀርምና ነው፡፡ ጓደኛውን ወይም ጎረቤቱንም እንደ ራሱ የሚወድ፣ ለእርሱ ደስ የሚያሰኘውንና የሚያስፈልገውን ሁሉ ለሌላው እንደሚያስፈልገው አድርጎ ስለሚቆጥር ወይም ስለሚያስብ እነዚያን የብሉይ ኪዳን መለኮታዊ ሕጎች ለመፈጸም የሚችልበትን አቅም ሊያገኝ ይችላል፡፡

አሁን ባለችው ዓለም ይህ ወርቃማ ትዕዛዝ ወይም ሕግ በሰው ሁሉ ዘንድ ተግባራዊ መሆን ችሉ ቢሆን ኖሮ፣ የዚህች ዓለም መልክ ምንኛ በተቀየረ ነበር! እንደሚታወቀው በየዘመናቱ ሰላምንና ጸጥታን ለማስጠበቅ ኃይልን መጠቀም የግድ ሆኗል፤ ፖሊስ፣ ወታደር፣ ዳኛ፣ ፍርድ ቤትና የመሳሰሉ ተቋማት በሰዎች መኻከል ይብዛም ይነስም ፍትህና ፍርድ እንዳይጓደል በሰዎች የተመሠረቱ ተቋማት ናቸው፡፡ ምናልባትም ሰው ሁሉ ግን ይህ መለኮታዊ ሥርዓት ገብቶት ወይም ከነፍሱ ጋር ተዋህዶት ቢሆን ኖሮ እነዚህ ተቋማት ጭራሽ አስፈላጊ ባልሆኑ ነበር፡፡

ሰው በተፈጥሮው የራስ ወዳድነት ባህርይ ስላለው ማናቸውንም ነገር ለሌላው ከማድረግ ወይም ለሌላው ቅድሚያ ከማሰብ ይልቅ ራሱን ያስቀድማል፡፡ ይህ ወርቃማ ሕግ ደግሞ በሰው ውስጥ ሕያው መሆን የሚጀምረው ሰውየው በክርስቶስ በሆነው ሕያው ሥራ በሩሉ ፍላጎትና መብት ሲሞትና ክርስቶስ በሰውየው ውስጥ ሕያው መሆን ሲጀምር ነው፡፡ ጌታ ያደረገውንና የሆነውን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፣ በዚህ ምድር ላይ ሊገኝ የቻለው ለሰው ደስታ ነው፤ የሰውን ልጆችን ከአባቱ ጋር ያስታርቅ ዘንድ ከነበረበት ክብርና ማንነት በብዙ መልኩ ወደታች መውረድ ነበረበት፡፡ እናም ለእኛ ደስታ ኖሮ ዛሬ ያገኘነውን ነፃነት አጎናጸፈን፡፡

# አስተያየት

አስቀድሜ ይህን ርዕስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስደህ እንድትጽፍ የረዳህን እግዚአብሔርን ስለ አንተ አመሰግንዋለሁ:: ይህ መጽሐፍ ቀለል ባለ ቋንቋ የተጻፈ፣ የስብከትና የትምህርትን ዘይቤ አቀላቅሎ የያዘና ምሳሌዎችን አባባሎችን ለገለፃው በሚያመች መልክ ያከተተ በመሆኑ አንባቢው ሳይሰለች ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይረዳዋል ብዬ አስባለሁ::

ወደ ፊትም ይህ ትምህርት በተለየ ሁኔታ አማኞችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ በአጭርና በረጅም ኮርሶችና ሴሚናሮች ቢሰጥ ለማስተማሪያነት ያገለግላል ብዬ አምናለሁ:: በተለይም ከመሠረታዊው የደኅንነት ትምህርት ቀጥሎ አማኞች በክትትል ቢማሩት የጠራ የጌታ ደቀ መዛሙርትን ለማፍራት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋልና በዚህ መልክ ለማገልገል እንድትችል ከአሁኑ ብታስብበት እላለሁ::

በተረፈ አምላክ እግዚአብሔር የቃሉን መገለጥ እንዲሰጥህና ሌሎችም መጻሕፍት በመጻፍ አማኞችን ማገልገል እንድትችል ፀጋውንና ጥበቡን እንዲያበዛልህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየጸለይኩልህ በርታ እልሃለሁ::

ክፍሉ ኃይለማሪያም

ይህ መጽሐፍ ታትሞ ወደ አንባቢያን እንዲደርስ
በተለያየ መንገድ ድጋፍ ያደረጉ ሁሉ
እግዚአብሔር አምላክ ይባርካቸው::

© መርዓዊሥላሴ ንጉሤ

Merawislassie Nigussie

Telephone 251 911 215882

P.O.Box 952

E-mail selihom2002@yahoo.com

Addis Ababa Ethiopia